የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም የምዕራፍ ሁለት ጥያቄዎች

፩-ጳውሎስ ማለት ምን ማለት ነው?

፪-የቅዱስ ጳውሎስ መጠሪያ ስሞችን ፭ ዘርዝሩ?

፫-የቅዱስ ጳውሎስ የቀድሞ ስሙ ማን ይባላል?

፬-ቀዳሜ ሰማዕት ሲወገር የወጋሪዎቹን ልብስ የያዘው ማነው?

፭-እግዚአብሔር ለቅዱስ ጳውሎስ"ለምን ታሳድደኛለህ"ብሎ የተገለጠለት በየት ቦታ ነው?

፮-ቅዱስ ጳውሎስን አስተምሮ ያጠመቀው ማነው?

፯-ቅዱስ ጳውሎስ የኦሪትን ትምህርት ከማን ተማረ?

፰-ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ሲያስተምር ሁለት ፈተናዎች ገጥመውታል ምንና ምን ናቸው?

፱-ቅዱስ ጳውሎስ ከ፲፪ ሐዋርያት ልዩ የሚደርገው ምንድ ነው?

፲-ቅዱስ ጳውሎስ በየትኛው ቁሳር ?.....

በየትኛው ወር እና ቀን?.....

በስንት ዓ.ም ተመተረ?.....

ስንት መልእክታትንስ ጻፈ?.....

፲፩-ቤተክርስቲያንን ቅዱሳን ሐዋርያትን በምን አይነት መንገድ ታከብራቸዋለች?

፲፪-ዘመነ ሐዋርያነ አበው የሚባለው ከስንት ዓ.ም እስከ ስንት ዓ.ም ነው?

፲፫-ዘመነ ሐዋርያነ አበው ለምን ተባለ?

፲፬-የመሸጋገሪያ ዘመንስ ለምን ተባለ?

፲፭-በዘመነ ሐዋርያነ አበው ከተነሱ ቅዱሳን ሦስቱን ጥቀሱ?

፲፮-ቅዱስ አግናጥዮስ የማን ደቀ መዝሙር ነበር?

፲፯-አግናጥዮስ ማለት ምን ማለት ነው?

፲፰-ቅዱስ አግናጥዮስ.....ዓ.ም ታሕሳስ.....ሰማዕትነትን ተቀበለ፡፡

፲፱-ቅዱስ ቀሌምንጦስ ከሐዋርያነ አበው ልዩ የሚደርገው?

፳-ቅዱስ ቀሌምንጦስ በሕዳር.....ሰማዕትነትን ተቀበለ፡፡

፳፩-ቅዱስ ፖሊካርፕስ.....ዓመቱ.....ዓ.ም የካቲት.....ሰማዕትነትን ተቀበለ፡፡

የምዕራፍ ፫ ጥያቄዎች

፳፩-ዘመነ ሰማዕታት የሚባለው ከስንት ዓ.ም እስከ ስንት ዓ.ም ነው?

፳፩-ሰማዕት ማለት ምን ማለት ነው?

፳፪-ሰማዕትነት በስንት ወገን ነው ዘርዝሯቸው?

፳፫-የሮም ቄሳሮች በምን ምክንያት ነው ቤተክርስቲያን ላይ መከራ ያመጡት?

፳፬-በዘመነ ሰማዕታት የመጀመሪያውን መከራ በቤተክርስቲያን ያመጠው ቄሳር ማነው?

፳፭-በዘመነ ሰማዕታት ክርስቲያኖች የሚሸሸጉበት ግበበ ምድር/ፍልፈል ዋሻ/ ለክርስቲያኖች ከመሸሸጊያ ውጭ ለምን ይጠቀሙበት ነበር?

፳፮-በሮም ከነገሡ ቄሳሮች በቤተክርስቲያን ላይ ከፍተኛውን መከራ ያመጣው ቄሳር ማነው?

፳፯-ድዮቅልጥያኖስ ለምን ክርስቲያኖችን አምርሮ ጠላ?

፳፰-ድዮቅልጥያኖስ በቤተክርስቲያን ላይ ያወጃቸው አዋጆች ፫ቱን ጥቀሱ?

፳፱-በሮም ከነገሡ ቄሳሮች ድዮቅልጥያኖስን ምን ይለየዋል?

፴-የዘመነ ሰማዕታት የመጨረሻው ሰማዕት ማን ይባላል?

፴፩-የጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናትና አባት ስማቸው ማን ይባላል?

፴፪-ቆስጠንጢኖስ ማለት ምን ማለት ነው?

፴፫-ጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን ያጠመቀው አባት ማን ይባላል?

፴፬-ጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን ከሰጣቸውን መብቶች(ያበረከተው አስተዋጽኦ) 5ቱን ዘርዝሩ?

፴፭-ንግሥት ዕሌኒ ለቤተክርስቲያን ያበረከተችው አስተዋጽኦ ዘርዝሩ?

፴፮-ንግሥት ዕሌኒ ዕረፍቷ መች ይታሰባል? ወሩና ቀኑ

፴፯-ጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዕረፍቱ መቼ ይታሰባል? ወሩና ቀኑ

፴፯-ከግኖስቲኮች ትምህርት(አመለካተከት) 3ቱን ጥቀሱ?

የምዕራፍ ፬ ጥያቄዎች

፩- የቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመን (ዘመነ ሊቃውንት) መባሉ ስለምንድ ነው?

፪-በዘመነ ሊቃውንት ከተነሱ አባቶች 5ቱን ጥቀሱ?

፫-ባስልዮስ ማለት ምን ማለት ነው?

፬-ለመጀመሪያ ጊዜ የነዳያንን ሆስፒታል በ4ተኛው መቶ/ክ/ዘመን ያስገነባው አባት ማን ይባላል?

፭-ቅዱስ ባስልዮስ ካደረገው ተአምራት 3ቱ ጥቀሱ?

፮-የውዳሴ ማርያም ደራሲ አባት ማን ይባላል?

፯-ቅዱስ ባስልዮስ ለቤተክርስቲያን ያበረከተው አስተዋጽኦ ዘርዝሩ?

፰-ቅዱስ ኤፍሬም ዕረፍቱ መች ይታሰባል?

፱-ቅዱስ ባስልዮስ ዕረፍቱ መች ይታሰባል?

፲-ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በየት ሀገር ተወለደ?

፲፩-የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እናቱ እና አባቱ ማን ይባላሉ?

፲፪-ቅዱስ ዮሐንስ "አፈወርቅ" ለምን ተባለ?

፲፫-ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የካህናት ማዕረግ የላቀ መሆኑን ያስረዳበት ሥራ የቱ ነው?

፲፬-ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለቤተክርስቲያን ያበረከተው አስተዋጽኦ ዘርዝሩ?

፲፭-ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዕረፍቱ መች ይታሰባል?በስንት ዓመቱስ ዐረፈ?

፲፮-ድሜጥሮስ ማለት ምን ማለት ነው?

፲፯-ቅዱስ ድሜጥሮስ በየት ተወለደ?

፲፰-የቅዱስ ድሜጥሮስ ሚስቱ ማን ትባላለች?

፲፱-ቅዱስ ድሜጥሮስ ለቤተክርስቲያን ያበረከተው አስተዋጽኦ ዘርዝሩ?

የምዕራፍ ፭ እና ፮ ጥያቄዎች

፩-ሁለቱ የትርጓሜ ትምህርት ቤቶችን የሚባሉት እነማን ናቸው?

፪-የእስክንድርያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት መስራች ማን ይባላል በስንት ዓ.ም ተመሰረተ?

፫-የአንጾኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት መስራች ማን ነው?

፬-ሦስቱ የቤተክርስቲያን ዓለማቀፍ ጉባዔዎች የሚባሉትን ዘርዝሩ?

፭-ጉባዔ ኒቅያ በስንት ዓ.ም ተደረገ?

፮-በኒቅያ ጉባዔ እዲሰባሰቡ ለአባቶች ጥሪ ያቀረበው ንጉሥ ማን ይባላል?

፯-ለጉባዔ ኒቅያ መሰባሰብ ምክንያት የሆነው መናፍቅ ማን ይባላል አስተምሮስ ምን ነበር?

፰-በኒቅያ ጉባዔ የተገኙት አባቶች ስንት ናቸው?

፱-የኒቅያ ጉባዔ በሊቀ መንበርነት እና በጸሐፊነት ያገለገሉ አባቶች ማን እና ማን ናቸው?

፲-318ቱ ሊቃውንት አርዮስን ካወገዙ በኋላ ስንት ቀኖናዎችን ደነገጉ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ምን አስተዋጽኦ አደረጉ?

፲፩-ጉባዔ ቁስጥንጥንያ በስንት ዓ.ም ተደረገ?

፲፪-በጉባዔ ቁስጥንጥንያ እዲሰባሰቡ ለአባቶች ጥሪ ያቀረበ ንጉሥ ማን ይባላል?

፲፫-ለጉባዔ ቁስጥንጥንያ መሰባሰብ ምክንያት የሆነው መናፍቅ ማን ይባላል? አስተምሮስ ምን ነበር?

፲፬-በጉባዔ ቁስጥንጥንያ የተገኙ አባቶች ስንት ናቸው?

፲፭-በጉባዔ ቁስጥንጥንያ የተገኙ አባቶች መቅዶንዮስን ካወገዙ በኋላ ለቤተክርስቲያን ያበረከቱት አስተዎጽኦ እንዲሁም ስንት ቀኖናዎች ደነገጉልን?

፲፮ጉባዔ ኤፌሶን በስንት ዓ.ም ተደረገ?

፲፯-በጉባዔ ኤፌሶን እንዲሰበሰቡ የጠራው ንጉሥ ማን ይባላል?

፲፰-ለጉባዔ ኤፌሶን መሰባሰብ ምክንያት የሆነው መናፍቅ ማን ይባላል?አስተምሮስ ምን ነበር?

፲፱-በጉባዔ ኤፌሶን የተገኙ አባቶች ስንት ናቸው?

፳-የኤፌሶን ጉባዔ ሰብሳቢ አባት ማን ይባላል?

፳፩-በጉባዔ ኤፌሶን ስንት ቀኖናዎች ተደነገጉ?